**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**

# ‹‹አሽባሪ›› ጭንቀት የወለደው የህወሃት/ኢህአዴግ ምርቃት!!

*ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ድርጅታዊ መግለጫ!!*

ሰብዓዊ ፍጡር የሆነ ሁሉ ‹‹እውነት››፣ ‹‹ዕርቅ›› እና ‹‹ፍትሕ›› የሚባሉት ጽንሰሃሳቦች ዓለምአቀፋዊነት ያላቸው መርሆዎች እንጂ አካላዊ ስብዕና የተላበሱ እንዳልሆኑ በውል ይረዳል፡፡ ነገር ግን እነዚህ መርሆዎች ስብዕና ቢኖራቸው ኖሮ ህወሃት/ኢህአዴግ ‹‹በአሸባሪነት›› ወንጅሏቸው በአሁኑ ጊዜ በእስር ይማቅቁ ነበር፡፡ ምክንያቱም ‹‹እውነት›› **የአገዛዙን ጭከና፣ መጠን የለሽ ሙስና፣ የመብት ጥሰት፣ ወዘተ ያጋልጣልና፤ ‹‹ዕርቅ›› ደግሞ አገዛዙ የሚከተለውን የከፋፍለህ ግዛ መመሪያ በማምከን አንድነትን ያመጣልና፤ ‹‹ፍትሕ›› በሌላው ወገን ደግሞ ለንጹሐን ነጻነትን ለግፈኞች ደግሞ ፍርድን ይሰጣልና ነው፡፡** ከዚህ በመነጨ እሳቤና እነዚህን መርሆዎች በመመርኮዝ የሚንቀሳቀሱ ዜጎችን አገዛዙ እየተከታተለ በምክንያት ሊያጠፋቸው ሲጣደፍ የሚታየውም ለዚህ ነው፡፡ በቅርቡም የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ የጋራ ንቅናቄያችንን ዋና ዳይሬክተር አቶ ኦባንግ ሜቶን ‹‹አሸባሪ›› በማለት ‹‹ክስ›› ያቀረበባቸውም በዚሁ የእምነቱ መነሻና ድምዳሜ ጭምር ነው፡፡

የጋራ ንቅናቄያችን ይህንን መሠረተቢስ እና ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ክስ በቀላሉ የሚመለከተው አይደለም፡፡ ለሕግና ለሥርዓት መከበር ካለን ጠንካራ እምነት በመነሳት የጋራ ንቅናቄያችን ሥራ አስፈጻሚ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ይህንን ዓይን ያወጣ ‹‹ክስ›› ድርጅታችን የሚቻለውን ያህል መንገድ በመሄድ ይታገለዋል፡፡ ፍረጃው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከበርካታ ዓመታት ጀምሮ እስከ አሁን እያካሄደ ያለውን የአሸባሪነት ተግባር በተለያየ መልኩ ለተለያዩ አካላት በማጋለጥ በጽናት እንድንታገልና ይህ አገዛዝ ከኢትዮጵውያን ጫንቃ ላይየሚወገድበትንም መንገድ ለማመቻቸት በምናደርገው ትግል የበለጠ እንድንተጋ አድርጎናል፡፡

በግልጽ እንደሚታወቀውና በሕገ ደንባችን በማያወላውል መልኩ እንደተቀመጠው **ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ከማንም ያልወገነ፣ ፖለቲካዊ ያልሆነ ነገር ግን በኢትዮጵያ የማኅበራዊ ፍትሕ መስፈን በሰላማዊ መንገድ የሚታገል ድርጅት ነው፡፡** ይህንን የድርጅታችን አቋም የተለያዩ በአገር ውስጥና በውጪ ያሉ ወገኖች ብቻ ሳይሆኑ ራሱ ህወሃት/ኢህአዴግ እንዲሁም አቶ መለስ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ለዚህም ነው ህወሃት/ኢህአዴግ የጋራ ንቅናቄያችንን መሪ አቶ ኦባንግ ሜቶን ‹‹አሸባሪ›› ብሎ ‹‹ሲወነጅል›› ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄን ግን በስም ‹‹አሸባሪ ድርጅት›› ብሎ ያልጠቀሰው፡፡ ይህ ሁኔታ ‹‹አልሸሹም ዞር አሉ›› ቢያስመስልም ግን የጋራ ንቅናቄያችን የቆመለት ዓለምአቀፋዊ ዓላማ ህወሃት/ኢህአዴግንና መሪውን እንዴት እንደሚያሸብራቸው በግልጽ ያሳየ ለመሆኑ ከቶውንም ጥርጥር የለንም፡፡ ባይሆንማ ኖሮ አስቀድሞ የጋራ ንቅናቄያችንን ‹‹አሸባሪ ድርጅት›› በማለት ራሱ በሙላት በተቆጣጠረው ‹‹ፓርላማ›› አስወስኖ ሲያበቃ አቶ ኦባንግ ሜቶን ‹‹የአሸባሪው ድርጅት መሪ›› በማለት ‹‹መወንጀል›› ይችል ነበር፡፡ ወይስ ይህንን ጉዳይ ከዚህ በፊት እንዳደረገው ራሱ ለፈጠረው ‹‹ፓርላማ›› ቢያቀርብ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ኀቡዕ ‹‹የፓርላማ›› አባላት የተቃውሞ ድምጽ ይሰጣሉ ብሎ ፈርቶ ይሆን?

ህወሃት/ኢህአዴግ ቀደም ሲል በበረሃ በነበረበት ወቅት በተለያዩ ጊዜያት የአሸባሪነት ተግባራት መፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ ስሙም በአሸባሪነት መመዝገቡ ዓለም የሚያውቀው እውነት ነው። የፈጸማቸው የአሸባሪነት ተግባራትም፡- የውጭ አገር የዕርዳታ

ሰጪና የሃይማኖት ሠራተኞችን ማፈን፣ አንዳንዶችንም መግደል፣ ለዕርዳታ የተሰጠ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ከረሃብተኛ አፍ ላይ በመንጠቅ እጅግ በርካታዎች በረሃብ እንዲፈጁ ማድረግ፣ ገንዘቡንም ወስዶ ለጦር መሣሪያ ግዢ ማዋል፣ ‹‹ሓርነት አወጣዋለሁ›› ብሎ በተነሳለት ሕዝብ ላይ ሆን ብሎ ጭፍጨፋ እንዲካሄድ በማነሳሳትና በሚደርሰውም የሰው ዕልቂት ለራሱ እኩይ ዓላማ ማዋል፣ ወዘተ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

አብዛኛው የትግራይ ተወላጅ እንደሚያውቀውና የኢትዮጵያ ሕዝብም እንደሚመሰክረው የሐውዜን ዕልቂት በደርግ ተዋጊ ጀቶችና ሔሊኮፕተሮች የተፈጸመ ቢሆንም **ጭፍጨፋውን በረቀቀ ሁኔታ ያቀነባበሩትና ያነሳሱት የያኔዎቹ የህወሃት አመራሮች በአሁኖቹ ‹‹የመንግሥት›› ባለሥልጣናት መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡** ቀኑ የገበያ ቀን የነበረ በመሆኑ በጥቃቱ ከሦስት ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል፤ በገበያው የነበሩ እጅግ በርካታ እንስሶችና ከብቶች አልቀዋል፤ እንዲያውም ከአንድ ቤት እስከ ሰባት የቤተሰቡ አባላት መሞታቸው ይነገራል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም - በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩ የትግራይ ተወላጆችን ‹‹አፍቃሪ ደርግ›› ናቸው በማለት የተለያየ የአሸባሪነት ተግባር በማቀነባበር በደርግ እንዲታሰሩ ወይም እንዲገደሉ ወይም ከአገር እንዲኮበልሉ፣ ወዘተ ሲያስደርግ የነበረው አሸባሪ ማነው? ‹‹የትጥቅ ትግሉን አይደግፉም›› ተብለው በመፈረጅ እንደ ሐውዜን ዓይነቶቹ ከተሞች ላይ ዕልቂት እንዲደርስ ያቀነባበረውስ የአሸባሪ ቡድንና መሪው ማነው? በግፍ የተጨፈጨፉት ንጹሐን ደም ይጮኻል፤ አጽማቸውም ይናገራል፤ ወንድሞችና እህቶቻቸው ያመረቀዙት ሮሮ የሚገነፍልበት ወቅትም ደርሷል፡፡ ስለሆነም ይህንን በውል የሚረዳው ህወሃት/ኢህአዴግና መሪው በተለያየ መልኩ የሚፈራገጡትም ለዚሁ ነው፡፡

ከአምስት ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ በሚኒባሶች ላይ ቦምብ ፈንድቶ ንጹሕ ኢትዮጵያውያን ሲሞቱ ህወሃት/ኢህአዴግ ‹‹አሸባሪው የኦሮሞ ነጻነት ግምባር (ኦነግ) ነው ይህንን የፈጸመው›› በማለት ራሱ ከተቆጣጠረው የዜና ማሰራጫ አልፎ በዓለምአቀፍ የዜና አውታሮች ሲያስለፍፍ ከርሞ ነበር፡፡ ሆኖም በቅርቡ የወጣው የሹልክዓምድ (ዊኪሊክስ) ዘገባ ይህንን የቦምብ ፍንዳታ ራሱ ህወሃት/ኢህአዴግ እንዳቀነባበረውና እንዳስፈጸመው አስነብቦናል፡፡ ይህም የያኔውን የበረሃ አሸባሪ ራሱን አግዝፎ በ‹‹የመንግሥት›› አሸባሪነት ደረጃ የተቀመጠና ያኔም ሆነ አሁን የሚመራው በአቶ መለስ መሆኑ ፈጽሞ የማያጠራጥር ሆኖ ሳለ በአንጻሩ ግን የምዕራባውያንን ቀልብ ለመሳብና የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘምም ይህንኑ የአሸባሪነት ስልት ሲጠቀም በቅርቡ በገሃድ ያየንበት ተግባሩ ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ‹‹አሸባሪ›› የሚለው ቃል ከስሙ በፊት እንደ ማዕረግ እንደሚለጠፍ የማይቀር ሐቅ እየሆነ መጥቷል፡፡ በተለይም ከዚህ በፊት ‹‹በአሸባሪነት›› ተከስሰው በእስር የሚማቅቁትንና ከአገር የተሰደዱትን እያሰብን ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ የዳዊት ከበደና የአቤ ቶኪቻው ከአገር መሰደድ አገዛዙና በውስጡ ያሉት አመራሮች ራሳቸው በከፍተኛ ሽብር ውስጥ ለመሆናቸው ሌላ ማስረጃ የሰጠ ሐቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጋዜጠኞች ብቻ አይደሉም ሃሳባቸውን በነጻነት በመናገራቸው፣ ለእውነት በመቆማቸው፣ ለፍትሕ በመታገላቸው ከአገራቸው የተሰደዱ፣ በእስር የሚማቅቁ፣ በሥራ አጥነት የሚንገላቱ፣ ወዘተ ኢትዮጵያዊ የጤና ባለሙያዎች፣ መሃንዲሶች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ ጸሐፊዎች፣ ደራሲዎች፣ ባለሥልጣናት፣ አስተዳዳሪዎች፣ የባንክ ሠራተኞች፣ የግል ባለሃብቶች፣ ተጣጥሮ አዳሪዎች፣ መምህራን፣ ወዘተ ተጠቅሰው የማያልቁ እጅግ በርካታ ዜጎቻችን በአገራቸው እንደ ባለሙያና እንደ ሰው ተከብረው ለመኖር የሚበቁበትን ጊዜ ቀርቧል፡፡

## ለእነዚህ የፈጠራ ‹‹ክሶች›› የምንሰጠው ምላሽ ምንድነው?

ራሱን በእሳት በማቃጠል የሰዋው **ወንድማችን የኔሰው ገብሬ መስዋዕትነቱን የከፈለው ለተወሰነ የዘር ክፍል፣ ሃይማኖት፣ ክልል፣ ጾታ፣ የፖለቲካ ቡድን፣ ወዘተ አልነበረም፤ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ እንጂ፡፡** ይህ ድርጊቱም የኢትዮጵያውያን መከራ የደረሰበትን ጫፍ

ከማመላከቱ በተጨማሪ ‹‹ከዘር (ከማንኛውም ልዩነት) በፊት ሰብዓዊነት የሚቀድምባትን አዲሲቷ ኢትዮጵያ›› ትመሰረት ዘንድ ተግተን እንድንሠራ ለሁላችንም ኃላፊነት ትቶልን አልፏል፡፡ ለእውነት፣ ለፍትሕ፣ ለነጻነት፣ ለዕርቅ በመቆም ከጥቂቷ ነገር ጀምረን እነዚህን መርሆዎች በአገራችን እውን እስኪሆኑ በመትጋት የኔሰውን ህያው ልናደርገው ይገባናል፡፡

ከበርካታ ዓመታት በፊት በጋምቤላ አካባቢ በሚገኙት አኙዋኮች ላይ በአቶ መለስ የሚመራው የመከላከያ ሠራዊት የዘር ማጥፋት አሰቃቂ ተግባር ሲፈጽም፤ በትውልድ አኙዋክ የሆኑት የጋራ ንቅናቄያችን መሪ አቶ ኦባንግ ሜቶ እጅግ በርካታ የቅርብ ቤተሰቦቻቸው የተገደሉባቸው ቢሆንም ዓመጽን በዓመጽ ለመመለስ በበቀል አልተነሱም ነበር፡፡ የህወሃት ጦር እነዚያን ንጹሐን ወገኖቻችንን ሲጨፈጭፍ፣ ሲያሰቃይ፣ አስገድዶ ሲደፍር፣ ከአገር ሲያባርር፣ ወዘተ ሁኔታው ማንንም ለበቀል እርምጃ እንደሚያነሳሳ እሙን ነው፡፡ ሆኖም ግን አቶ ኦባንግ ‹‹የወገኔን ደም እበቀላለሁ›› በማለት ለዓመጽ ድርጊት የዓመጽ መልስ ሳይሆን የሰጡት ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነቱን ሳይጎናጸፍ የአኙዋክ ሕዝብ ለብቻው ዘላቂነት ያለው ነጻነት ሊያገኝ አይችልም፤ ለአኙዋክ መብት ብቻ ልቁም ቢባል እንኳን መንገዱ ህወሃት የሄደበት ዓይነት ፈጽሞ መሆን የለበትም›› በማለት ነበር ለሰላማዊ ትግል የተሰለፉት፡፡ የዚህ ሰላማዊ ትግል መመሪያም አሸባሪነት፣ ቦምብ ማፈንዳት፣ ድልድይ ማፍረስ፣ ለገበያ የወጣ ሕዝብ ማስጨፍጨፍ፣ ዘር ማጥፋት፣ አስሮ ማሰቃየት፣ ሃብት መዝረፍ፣ ወዘተ አይደለም፡፡ በተጻራሪው ‹‹ከጎሣ ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ እንስጥ›› እንዲሁም ‹‹ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ማንም ነጻ ሊሆን አይችልም›› የሚል ነው እንጂ፡፡ አቶ ኦባንግ ሜቶ ለእንደዚህ ዓይነቱ ዓለምአቀፋዊ መመሪያ የቆሙ፣ ለፍትሕ የሚታገሉ፣ ለዕርቅ የቆሙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ‹‹ለትግራይ ተወላጆች ቆሜአለሁ›› የሚለውን ህወሃትን የመጀመሪያ ሰልፈኛ ሆነው መቃወምና መታገል ያለባቸው ራሳቸው የትግራይ ተወላጆች ናቸው ብሎ የጋራ ንቅናቄያችን ያምናል፡፡ ሌላው ኢትዮጵያዊ ነጻ ሳይወጣ እነ አቶ ስብሃትና መለስ የሚደግሱት የትግራይ ነጻነት እውን ሆኖ የደስታ ከበሮ ይደለቃል ብሎ የሚያስብ የትግራይ ተወላጅ ህወሃት ያቀናበረለትን ሸብር የማያስተውል ብቻ ነው፡፡ ከበረሃው ትግል ጀምሮ ህወሃት ለትግራይ ሕዝብ ፈጽሞ እንዳልቆመ በተደጋጋሚ ማሳየቱን የሚያስተውል የትግራይ ተወላጅ በሙሉ ከአሸባሪው ህወሃት ጋር ሳይሆን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚቆምበት ጊዜ አሁን ነው፡፡ ዛሬ ‹‹በመንግሥትነት›› ሥልጣን ላይ የተቀመጠው ይህ አሸባሪ ድርጅት እጅግ በርካታ የትግራይ ተወላጆችን ከበረሃ ጀምሮ እስከ ድል ማግስት ሰውቷል፡፡ ወደፊትም ‹‹አካሄዴን ይቃወማሉ›› የሚላቸውን ለማስወገድ መንገዱን አመቻችቷል፡፡ ይህንን ሁሉ የሚያደርገው በትግራይ ተወላጆች ስም በመሆኑ እያንዳንዱ የትግራይ ተወላጅ የድርጊቱ ግምባር ቀደም ተቃዋሚ በመሆን ቀኑ ከመምሸቱ በፊት ከመላው ኢትዮጵያዊ ጋር ሊቆም እንደሚገባው የጋራ ንቅናቄያችን አጥብቆ ያሳስባል፡፡ ለእውነት፣ ለፍትሕ እና ለዕርቅ ‹‹የወያኔ ሓርነት›› እንቅስቃሴ ማድረግ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን በተለይ ከትግራይ ሰዎች በቀዳሚነት ይጠበቃል፡፡

ይህንን ‹‹የአሸባሪነት›› ተግባር በመፈጸም በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ‹‹ፍርድ እንደ ውኃ፤ (ምህረትም) እንደማይደርቅ ፈሳሽ›› አስኪፈስ ድረስ ለእውነት፤ ለፍትሕና ለዕርቅ እንቁም፡፡ ፈጣሪም ይርዳን፡፡

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ (smne@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

